# የተቃዋሚ ድርጅቶች በቀጣዩ ምርጫ ቢሳተፉ ጥቅሙ ምንድነው? ጉዳቱስ?

በመሰረቱ የአፍሪካ መሪዎች: ምርጫ የሚባል ነገር: በፍጹም አይመቻቸውም:: ምርጫ እናድርግ እንኳን ቢሉ: በነሱ ታዛቢነት; በነሱ የምርጫ ቦርድ ተቋም: በነሱ የምርጫ ድምፅ ቆጣሪዎች: እና እነሱ በሚያዙት የፍርድ ተቋም: እና እነሱ በሚያዙት ሚዲያዎች ብቻ እንዲሆን ነው የሚፈልጉት:: እሩቅ ሳንሄድ: "ምርጫ 97" እንኳን ብናየው: ገዢው መደብ የህዝብን ድምፅ እንዴት ውጦ እንደቀረ ነው:: ሕዝቡም ድምጼ ይከበር ቢል እስካሁን ሰሚ አላገኘም:: እንግዲህ ይህ ሁሉ ሁኔታ ባለበት ሁኔታ ነው "ምርጫ 2002" ካለምንም እፍረት እየመጣሁ ነው የሚለን:: አጃኢብ ነው አለ ያገሬ ሰው:: ለነገሩ ዘመነ ሽቅብ ውስጥ አይደል ያለነው! መተፋፈርና መከባበር የጠፋበት ዘመን!

ብቻ: ለማንኛውም እኔ በግሌ 'ምርጫ 2002" አሁንም ለወያኔ ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ሊያስከትልበት ይችላል የሚል ግምት አለኝ:: አበው እንዲህ ብለው የለም: "ከምክር የለዩት ደብተራ ነገር ይሰራ" ጥሩ አባባል ነው:: አንድን ሰው ሲያርቁት ማሴሩ እንደማይቀር ነው አባባሉ የሚነግረን:: አንዳንድ ግዜም የአባቶቻችንን ምክር መስማቱ ጠቀሜታ አለው:: ከስህተታችን እንድንመለስ ይረዳናል:: እንግዲህ ከዚህ አንድምታ በመነሳት: ሜዳውን ሁሉ ለወያኔ ሰጥቶ: እንዲሁ ቢቆዝሙት: እያረሩ ከመኖርና: እድሜን ከማሳጠር ውጪ የሚያመጣው ፋይዳ አይታየኝም:: ውስጥ ሆኖ የባላንጣን አሰላለፍ እየገመገሙ: በመታገል ብቻ ነው ባላንጣን ማሸነፍ የሚቻለው:: ወያኔም ቢሆን: ስጋቱ አጠገቡ ላለው ባላንጣ እንጂ: ከሩቅ ርቀት ላይ ሆኖ እንደኔ በኮምፒይተር ላይ ለሚታገል ወገን አይደለም:: እንደኔ ከባህር ማዶ ላይ ሆኖ፡ የወገኑ ሰቆቃ አንገብግቦት የሚታገል ወገን: ሀሳብ በመጠቆም፤ ዲፕሎማሲያዊ ትግል በማድረግ (ሰሚ ካገኘ) እና ለድርጅት ስራ ማስኪያጃ ገንዘብ በማዋጣት ሊታገል ይችላል:: ነገር ግን አገር ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ካለመረዳት: በፓርቲዎች ድርጅታዊ አሰራር ውስጥ ገብቶ፡ ትዕዛዝ ለመስጠት መዳዳት በፍፁም ተገቢ አይደለም:: በባዕድ አገር ላይ በሚኖረው ወገን ላይም ክፍፍልን ከማስፋፋትና የህብን ጠኔ ከማራዘም ውጪ የሚያመጣው ፋይዳም የለም:: ይልቅ የዋህነታችንን ትተን: ተቃዋሚው ሀይል: የራሱንም አቅም ሆነ: የወያኔን የአሰላለፍ ሚዛን: እየገመገመ ለሚወስደው: እርምጃ መደገፍ አለብን:: "በዝምታ የለበት ሐሜታ" እንዳሉት አበው: መደገፍ እንኳን ባንችል: እውነተኛ የወገን ተቆርቋሪዎች ከሆንን አስተያየት ከመስጠት እራሳችንን ማገት ይኖርብናል:: ዝምታ በራሱ ወርቅ ነውና::

ለምሳሌ እምዬ ምንሊክ: ጠላትን ከትግራይ ምድር ካወጡት በሁዋላ: መረብን ተሻግረው ወደ ሐማሴን መሄድ ያልቻሉት: ወታደሮቻቸው ሶስት ወር ሙሉ ትግሬ ላይ በረሀብ ተጎድቶ ስለ ነበርና በሞተው ተክተን የከሳውን አወፍረን ከርሞ እንመለሳለን በማለት ወደ ሸዋ እንደተመለሱ ታሪክ ይነግረናል:: ነገር ግን እምዬ ምንሊክ: የአድዋውን ድል ተመርኩዘው: ጉዟቸውን ወደ ሀማሴን ቢያደርጉ ኖሮ: የኢትዮጵያችን ታሪክ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመተንበይ ነቢይ መሆን አያስፈልግም:: ያው እንደሌሎቹ የአለም አገሮች ነጻነት አልባ ህዝቦች ሆነን ነበር የምንቀረው:: ብቻ አሁንም ቀኑ አልመሸምና: እንደ እምዬ ምንሊክ አይነት መሪ ኢትዮጵያ እንድታገኝ: ሁላችንም በያለንበት: ማቅ ለብሰን አመድ ነስንሰን: ልንፀልይ ይገባል::

ነገርን ነገር ያመጣዋል እንዲሉ አበው: ከጳውሎስ ኞኞ መፅሀፍ ላይ ያገኘሁትን: እምዬ ምንሊክ ሲሞቱ የእምዬ ኢትዮጵያ ልጆች: ሀዘናቸውን እና ለቅሶዋቸውን: ለምንሊክ እንዲህ በማለት ነበር የገለጹት…

አጤ ምኒልክ ሲሞቱ
ምነው አትሔዱ ከፍታቱ::
እናንት ሰዎች ከፋታችሁ
አለማስቀበራችሁ::

አጤ ምኒልክ ንጉሡ
አባ ማቴዎስ ጳጳሱ

እንዴት ውላችኋል: ንጉሥ ወዴት ዋሉ
እስከ ጊዜው ድረስ ገበያ ነበሩ::

ዘመዶቹ እንሂድ እንግባ አገራችን
ምኒልክ ከሞተ እንጀራ አባታችን::

ጌታዬ ምኒልክ ጃኖ አለመንሁም፤

ቃኘው መኮንን ራሱ
ሄዱ ይላሉ ገሥገሡ::
እምብዛም አሽከር አልቀራቸው::
ሁሉም ተከተሏቸው::
የፈተፈቱበት ነከቶብኝ ጣትዎ::
የአለም መልክ ዥጉንጉርጉር
ነጭ ጥቁር እንደነብር
አይቻታለሁ በሰልፍ
በምኒል ጊዜ ስታልፍ::

ምኒልክ መጓዙን የምትጠይቀኝ
ፊትም አላለፈ ኋላም አይገኝ::

ምኒልክ ተክላችን ወዴት ጠፉ ካገር:
ሸዋ አዲስ አበባ ታይቶባቸው ነበር::

አርባ ስድስት ዓመት የገዛኸው ንጉሥ
እንዳለህም ስጠኝ ከሌለህም ላልቅስ::

በቅሎ አለመንሁም፤
አምና ነበር እንጂ ዘንድሮ የለሁም::

ምኒልክ ይወቁት አይኔ ጠፋልዎ፤

አልጫ መረቁ ወጡ ሰለቸኝ
ምኒልክ ተነስቶ ሽሮ ባበላኝ::

ያ ዳኘው ምኒልክ ሁዳዱን አስፍቶ
በየቦታው ተልሞ በየቦታው ተግቶ
ሳይጨርስ አረፈ አዝመራውን ትቶ::

እንግዲህ ለምኒልክ በወቅቱ የነበሩ ኢትዮጵያኖች: ይህንን ያህል ፍቅር ይሰጡ የነበረው: ካለምክንያት አልነበረም:: ለሕዝብ ቃል የተገዙ እና ፍርድ የማያጓድሉ ታላቅ ንጉስ በመሆናቸው ነው:: ታላቁ ንጉስ አጤ ቴዎድሮስ: ከዛም አጤ ዮሀንስ  ለብዙ ሺህ አመታት: በመሳፍንት አገዛዝ ተተብትባ: የነበረችውን ኢትዮጵያ: አንድ ለማድረግ በነበራቸው: ዕቅድ መሰረት (ባይሳካላቸውም) እምዬ ምኒልክ የነበራቸውን ልዩ የአመራር ክህሎት እና ጀግንነት በመጠቀም: እጅግ ፈታኝ የሆነውን የኢትዮያን አንድነት አንድ በማድረግ በድል የተዳጁ አልፋና ኦሜጋ (በአመራር ደረጃ ማለቴ ነው) ሊያሰኝ የሚችል ስም የያዙ ብቸኛ መሪ ናቸው:: ቅሉ: ምንያደርጋል: እምዬ ምኒልክ ልፋታቸው ከንቱ ሆኖ ነው የቀረው:: ምናልባት ከሳቸው በሁዋላ: በተወሰነ ደረጃ: ግርማዊ ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ: ብቻ ናቸው: የሳቸውን መንገድ የተከተሉት:: በይበልጥ ከጃንሆይ በሁዋላ የተፈጠሩት: መሪዎች: እጅግ ጨካኞች ከመሆናቸው ባሻገር: ለትውልዱ ጥላቻን ነው ያወረሱት::

ይህም ይመስለኛል ዛሬ: ልባችን ይቅርታ ለመስጠትም ሆነ ለመጠየቅ ያልታደለው:: ሌላው ቢቀር እንኳን አይኗ እየጠፋች ያለችውን አገራችንን ለማዳን በማሰብ ብቻ ይቅርታ ለመስጠትም ሆነ ለመጠየቅ አእምሮዋችንን ማሳመን ይገባን ነበር:: ነገር ግን እንደዛ አይነቱ ነገር እምብዛም አይታይም:: በፍፁም ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው::

ከላይ እምዬ ምኒልክን ለምሳሌነት: ያነሳሁት: የእሳቸውን ብልህነት በጥቂቱም ቢሆን: መጠቀም እንዳለብን ለማሳሰብ ነው:: የእምዬ ምኒልክን ታሪክ ስንረዳው: ፋሽስት ኢጣሊያን ያሸነፉት: በነበራቸው ብልህነት የተሞላው የአመራር ክህሎት በመጠቀም ነው:: ለምሳሌ እምዬ ምኒልክ የነበራቸውን አቅም ሳይገመግሙ: ወደ ሀማሴን ምድር ቢገሰግሱ ኖሮ: አሁን ላይ ሆነን በኩራት የምንናገረው: የአድዋ ድል: ሌላ ሊሆን ይችል ነበር:: ለዛ ነው እንግዲህ: ተቃዋሚዎች አቅማቸውን እየገመገሙ በሚወስዱት ድርጅታዊ ውሳኔ ላይ አንግባ የምለው:: ከወያኔ ማንነት የተነሳ: ተቃዋሚዎች ምንም አይነት ድርድር ባያደርጉ: የሁላችንም ምኞት ነበር:: ነገር ግን ማስተዋል የተሳነን ነገር ያለ ይመስለኛል:: ለምሳሌ አሁን ባለው የወያኔ አሰላለፍ: ተቃዋሚዎች ወደምርጫ አንገባም ቢሉ: ድሉ ለወያኔ ነው የሚሆነው:: በውጪ ያለውም ሆነ አገር ውስጥ ያለው ተቃዋሚ ምንም አይነት መሟገቻ ነጥብ አይኖረውም:: በውጪ ያለው ወገን ሰልፍ አዘጋጅቶ ለምዕራብ አገሮች አቤቱታውን ሊያሰማ ቢሞክር እንኳን: ሰሚ አያገኝም:: እነሱም ቢሆኑ: እናንተ ናችሁ እንጂ: ለህግ አልገዛም ያላችሁት: ገዢው መደብ አይደለም የሚል መልስ ነው የሚሰጡት:: የምዕራብ አገሮችም: ወያኔ በስልጣን: ላይ እንዲቆይ ከመፈለጋቸው አንድምታ የተነሳ: ስለወያኔ ሆነው: ተቃዋሚውን የሚረቱበት መከራከሪያ ነጥብ ይሆንላቸዋል:: ወያኔም ቢሆን የሚፈልገውም እቺን አይነቷን ነገር ነው:: ከእንደዚህ አይነቱ አካሄድም ወያኔ ብዙ ነገሮችን መጠቀም ይችላል:: ለምሳሌ ጥቂቶቹን ብናይ እንኳን:…

ሀ) ወያኔ አጋጣሚውን በመጠቀምም: ያኮረፈውን ድርጀት: በቀላሉ ሊያጠቃው ይችላል::
ለ) መሪዎቹ በአገር ውስጥ ተንቀሳቅሰው: ሕዝቡን እንዳያወያዩም: ዋስትና ያሳጣቸዋል::
ሐ) የፓርቲያቸውን: ወሳኝ ሰዎች ከቻለ ከሀገር በማሰደድ: ካልሆነም ደግሞ: በማስፈራራትና በማሰር: ፖለቲካዊ እንቅስቃሴያቸውን እንዲገድቡ ሊያደርግ ይችላል::
መ) በቅንጅት እንደተከሰተው: ዋናዎቹን መሪዎች በማሰር: በድርጅታቸው ውስጥ ክፍፍልን በመፍጠር: ተቀጥላ ድርጀት እንዲፈጠር መንገዱ ክፍት ሊሆንለት ይችላል::
ሠ) ተቃዋሚዎችም: ለምዕራብ አገሮች የሚያሰሙት አቤቱታ ለይስሙላም ቢሆን ሰሚ አያገኝም:: “በመሰረቱ የምዕራብ አገሮች ወያኔን ተቃዋሚዎች በምርጫ እንዳይሳተፉ ይመክሩታል የሚል ግንዛቤ አለኝ” ምክንያቱም እውነተኛ ሕዝብን ሊወክሉ የሚችሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች ከተሳተፉ እና ምርጫው ከተጭበረበረ፤ ሕዝባዊ ማጉረምረሙ እንደገና ሊያገረሽ ይችላል ከሚል ስጋት: ወያኔ: አሻንጉሊቶቹን: ተወዳዳሪዎች ብቻ ይዞ ወደምርጫ እንዲገባ ፍላጎታቸው ከመሆኑ የተነሳ: ነው::
ረ) ዋነኛው እና አብይ ጉዳይ: የወያኔ ካድሬዎች ሌት ተቀን የሚለፉበት: የተቃዋሚ ድርጅቶች ( ከአሻንጉሊቶቹ በስተቀር) ምርጫውን እንዳይሳተፉ (ደጋፊ በመምሰል) ቅስቀሳ ማድረግ ናቸው:: እዚህ ላይ እንዲሰመርበት የምፈልገው ነገር: ከዚህ በፊት ወያኔ ለሕዝብ ድምፅ ካለመገዛቱ የተነሳ: ከወያኔጋ የሚደረግ ምርጫ: “የተበላ ዕቁብ” ነው: ስለዚህ የተቃዋሚ ድርጅቶች ቀጣዩን ምርጫው አድማ ይምቱ የሚሉትን ወገኖች አያካትትም:: ይሁን እንጂ: እንደዚህ አይነቱ: አመለካከት ያላችሁ: አገር ውስጥ ያለውን ትግል እንደግፋለን የምትሉ ወገኖች: ከግብታዊነት በነጻ መልኩ: የወቅቱን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለደቂቃ ነገሩን እንድታሰላስሉት በዚህ አጋጣሚ ምክር ብጤ አቀርባለሁ::

ይህ እንዳለ ሆኖ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ወደምርጫ ቢገቡ: በብዙ መንገድ ስናየው ጠቀሜታው ከጉዳቱ ያይላል:: የድርጅታቸው ዋስትናም ሊጠበቅ ይችላል:: የድርጅታቸው ወሳኝ ሰዎች ባለችው አጋጣሚ እየተንቀሳቀሱ: ደጋፊዎቻቸውን ሊያወያዩ ይችላሉ:: ገዢውን መደብ መሞገቻ መከራከሪያ ነጥብም ይኖራቸዋል:: በእርግጥ ወያኔን መሞገቻ የሚሆኑ ብዙ ነጥቦችም: ቢኖሩም ቅሉ: ይህኛውንም እንደተጨማሪ መሟገቻ ነጥብ ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: በእርግጥ የዚህኛውን: ለየት ሊያደርገው የሚችለው: ገዢው መደብ ለቀጣዩ ምርጫ አልገዛም ቢል: ድፍን የኢትዮጰያ ሕዝብ የትጥቅ ትግልን እንደ አማራጭ ሊወስድ ስለሚችል: ገዢው መደብ: በዚህ ምርጫ የተቃዋሚ ድርጅቶች ባይሳተፉ መልካም ምኞቱ ነው:: የተቀዋሚ ድርጅቶችም: እንደው በደፈናው ከሚሆን: ከምርጫው በሁዋላ አቋማቸውን: እንዲያስተካክሉ ሊያግዛቸው የሚችል ወሳኝ ምርጫ ሊሆን ስለሚችል: በምርጫው መሳተፉ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠቀሜታው የጎላ ነው የሚሆነው::

ሌላው ደግሞ ሳልገልፅ የማላልፈው ነገር: የተቃውሞ ብትራችንን በተቃዋሚ መሪዎች ላይ ከማሳረፍ በወያኔ ላይ ሊሆን ይገባል:: ለምሳሌ አቶ ስዬን አስታኮ: በአነድነት ላይ የሚሰነዘረው: የከረረ ሄስ ወያኔን እንጂ ማንንም አይጠቅምም:: የአቶ ስዬም በአንድነት ውስጥ መግባት: የተከናወነው: አንድነት በድርጅቱ ውስጥ ባካተተው መርህዎ አማካኝነት ነው:: ነገሩን ለደቂቃ ብናስበው እንኳን፤ አቶ ስዬ ትግሉን መቀላቀላቸው: ከጉዳቱ ጥቅሙ ያመዝናል::

ለምሳሌ አብዛኞቻችን : የትግራይ ተወላጆች: በአደባባይ ወጥተው ወያኔን ሲቃወሙ አይታይም:: የትግራይ ህዝብ በአጠቃላይ ወያኔን ይደግፋል:: የሚል አመለካከት አለን:: በፍጹም ስህተት ነው:: በእርግጥ አብዛኛው የትግራይ ተወላጅ ወያኔን እንደሚደግፈው ሁሉ: በብዛትም የሚቃወመው አለው:: የሚቃወመውን ሀይል ለማሰባሰብ የተቃዋሚው ሀይል ከፍተኛ ጥረት ሊያደርግ ይገባዋል:: እኛም ብንሆን በጥሩ ቃላቶች በመታገዝ ወደተቃዋሚው ጎራ እንዲገቡ ጥረት ልናደርግ ይገባል:: ይህ እንዳለ ሆኖ: ይህንን ሀይል ለማሰባሰብ: እና በአደባባይ ወጥተው እንዲናገሩ: አቶ ስዬ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል የሚል አመለካከትም አለኝ::

ወደ ማጠቃለያው ሳመራውም: አቶ ስዬ ለቀጣዩ ምርጫ ወደ ተወለዱበት አገር ሄደው ለምርጫ ለመወዳደር ማሰባቸው ይበል የሚያሰኝ ነው:: የሳቸውም ወደ ትግሉ መቀላቀል: አዲስ አበባ ላይ ተወዳድሮ: ውጤት ያመጣሉ ተብሎ ሳይሆን የተፈለገው: ወደ ተወለዱበት አገር ሄደው: ገዢው መደብ እንደ እቃ እየተጫወተበት ያለውን ነፃነት

አልባውን የትግራይ ሕዝብ እንዲደርሱለት ነው:: እኔም በግሌ: አቶ ስዬ በወሰዱት ወሳኝ ፍልሚያ እያመሰገንኩኝ: ይቀናቸው ዘንድም ልባዊ ምኞቴን በዚህ አጋጣሚ በመግለፅ: ለዛሬ በዚህ እሰናበታለሁኝ::

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

ሕዝቅያስ ፍቅሬ- ከኬኔክትኬት
Agere_ethiopiaa@yahoo.com